# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 37 ቁጥር 8 ነሐሴ /መስከረም 2003 ዓ.ም


## ሞት ላይቀር መፈራገጥ

ነሐሴ 26 1967 የታወጀውን ኢሕአፓን ለማጥፋት ከቀይ ሽብር ፍጅት አንስቶ የጠባብ ብሔረተኛ ድርጅቶች ጦርነቶችም ተከፍተውበት እንደነበር የሚታወስ ነው። በ1983ም የወያኔና አጋሮቹ ጥቃት በሱዳንም፤ በሌሎች ባዕዳንም ታጅቦ እንደነበር የታየ ነው። የመለስ አገዛዝ ለሥልጣን ሲበቃም የኢሕአፓ አባላትን ወግቶና ገድሎ፤ መሪዎቹን አፍኖና ደብዛቸውን አጥፍቶ እንደነበር ይታወቃል። ተጠርጥሮ ለእስር የበቃ አንድም የኢሕአፓ አባል እስከዛሬ ፍርድ ቤት ወደሚባሉት አጠያያቂ ተቋሞች ለይስሙላ እንኳን አልቀረበም/አልቀረበችም። ወያኔ ሲመሠረት ጀምሮ በያዘው አጥፊ ዛር ዛሬም የሚያጓራ ነውና ኢሕአፓን አጠፋለሁ በሚል በኃይልም ሆነ በሁሉም መንገድ እየጣረ ነው። ከንቱ ልፋት ይሏል ይህ ነው !

ኢሕአፓ ከተመሠረተ 39፤ ከታወጀ ደግሞ 36 ዓመትን ያስቆጠረው ዓመት በመጣ ቁጥር ዓመት እየቆጠረ ሳይሆን እያንዳንዱን ቀን እየታገለና ሀገርና ሕዝብ የሚጠይቁትን መራራ ፅዋ እየጨለጠ ፤ እየተሰዋና መከራንም እየተቀበለ ነው። ኢሕአፓ ይህን ሁሉ ዓመት ቃል ኪዳኑን አክብሮና ህልውናውን ጠብቆ መገኘቱ ሊመሰገንና አርዓያም ሊሆን ሲገባ አንዳንዶች--ለባለጌ ገድሉ ውርደቱ ነውና--ድርጅቱ ለምን ፀንቶ ታገለ ፤ ሳይፈርስ ቆየ በሚል ሊከሱትና ሊወነጅሉትም በመጣር ላይ ናቸው። ደርግም ወያኔም ያፈሰሱትን ደም በስም ማጥፋትና ታሪክ ማርከስ ዘመቻ አጅበው የተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ዜጋ ሁሉ ያየው ነው። በተለይ ወያኔ አንዴም በራሱ የለየላቸው ከሀዲና ሀገር ገንጣይ መሪዎቹ አማካይነት አሊያም ባዕዳን የብዕር ባሮች በሚሏቸው ቅጥረኛ ታሪክ ፀሀፊ ነን በሚሉ አማካይነት የኢሕአፓን ታሪክ ለማጉደፍ ወረቀት በመጨረስ ላይ ናቸው። ኢሰፓው÷ ነፍስ ገዳዩ÷ የቀይ ሽብር ወንጀለኛው÷ አንጃውና የወያኔ ሎሌው ሁሉ በመለስ አገዛዝ አይዞህ አይዞሽ ባይነትና አሳታሚነት በድርጅቱ ላይ የሀሰት ታሪክ አቅራቢ ፅሁፎችን አዠጎድጉደዋል። ሐቅ በውሸት ከቶምና መቼምላይቀበር ከንቱ ልፋት !

መለስ ብለን በታሪክ በኢሕአፓ ላይ የቀረቡ አስገራሚ ክሶችን ብንመለከት ይህ ድርጅት ምንኛ ለሕዝብ ጠላቶች የእሳት አለሎ ሆኖ እንደባጀ ምስክር ይሆናል። የአረቦችም የአሜሪካም ቅጥረኛ ከመባል አልፎ ዝናብን አስቁሞ ድርቅ በማምጣትም ኢሕአፓ ተከሷል። ደርግያደረገውን የፍጅት ዘመቻንም በኢሕአፓ ላይ ለመጫን የሚጥሩ ዛሬም አሉ። ሥርዓቶቹ ብልሹ ሆነው የፈጠሩትንም የኤርትራ ችግር ሆነ የብሔረሰቦችን በደል የኢሕአፓ ጥፋት ነው ብለው የሚደርቁ ዛሬም ጥቂት አይደሉም። ሀሰት ሲደጋገም እውነት ይመስላል ነውና የሀገራችንን ሉ-

ላዊነትና ጥቅም አንዴም ቢሆን አሳልፎ ያልሰጠውን ኢሕአፓ ለመስኮብ አድሮ የነበረው ደርግና ለግራ ቀኙ ሀገርን የሸጠው ወያኔም ሳይቀሩ ኢሕአፓ ዚያድ ባሬንና የሶማሊያን ወረራ ደገፈ ብለው ዛሬም ይዋሻሉ/ያስዋሻሉ፡፡ የውሸትና አሉባልታን ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ መሠረት በዝርዝር በዚህ ለማቅረብ ባንቃጣም የውሸታም ሰው ማስታወሻው ጣቃ መሆኑን ሆነ ውሸት እያደር መቅለሉን የምናውቀው ነው፡፡ ሐቅን ተገን አድርጎ መታገልም ሆነ መቆምም ሲያቅት ወደ ውሸት ዘመቻ መሸጋገር የሁሉም ጨቋኝ አገዛዞች ጠባይ ነው፡፡ የመለስ አገዛዝ በ1997 ብዙ መቶ ዜጎችን ገድሎ በተገላቢጦሽ በሚቾቹና ጋቾቹ ላይ የቀረበውንና ዛሬም ለሚወስዳቸው የአፈና እርምጃዎች የሚያቀርባቸውን የሀሰት ማጠየቂያዎች መመርመሩ ብቻ ይበቃል፡፡ “ውሸት ደግ ነበር ጣጣው ባልነበር” ተብሏል፡፡ ሕዝብና ትዝታው፤ ሕዝብና ተመክሮው ዕወቀቱ አሉና ውሸት ሳይውል ሳያደር ይከስራል፤ ይጋለጣል፡፡ ህልውናውን አስከበሮ በትግል ፀንቶ ያለውን ኢሕአፓን ሕዝብ ያውቀዋልና በሀሰት ዘመቻና ክስ ለማጥፋት መጣሩ ልፋት ከንቱ ነው !

ኢሕአፓ ከሕዝብ አብራክ የተገኘ፤ በትግል ተወልዶ በትግል የኖረ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በፈሪ ዱላ የሚደማ ሆነ የሚሰበር አይደለም፡፡ ብዙ ብዙ ተሞክሮ ሁሉም ሴራ ከሽፏል፡፡ ኢሕአፓ ራሱን ለማሞገስ ሳይሆን የሕዝብ ቅርሰና ተቋም ነው--ለኢምንቶችና የታሪክ ሚዛናቸው ገለባ ለሆነው ወይም ለቆሸሸው አይንበረከክም፡፡ የሕዝብ ደም ጬኸት ምላሽ እንዲያገኝ፤ የፍትሕ ያለህ ጬኸቱም እንዲደመጥ ታግሏል፡፡ ሀገርን ግንባታ በጋራና በዴሞክራሲ፥ በሰላምና ዕርቅ ነው ብሎም ያደረገውን ጥረትና በደርግም በወያኔም የደረሰበትን ጥቃት ዜጎች በአብዛኛው ያውቃሉ፡፡ ለደርጉ የህብረት ግንባር ጥሪ በይፋ በዴሞክራሲያ ልሳኑ የሰጠው ምላሽ የእምቢታ ሳይሆን ሁሉን ያቀፈና ዴሞክራሲን መሠረት ያደረገ፤ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞችን መለቀቅ መንደርደርያ ያደረገ ይሁን የሚል ነበር፡፡ የደርጉ ምላሽ ግን ሰላማዊውን ትግል በጭፍጨፋ ማጥፋት እንደነበር ዛሬ የዚሁ አረመኔ ሥርዓት ርዝራዦች ሊክዱ ቢቃጡም በታሪክ የተጋለጠ ነው፡፡ ከዘረኛው ወያኔም ጋር የሰላምና ዕርቅ ጥረቶች ተደርገው ሁሉም ከሽፈው ለውይይት ወደ አዲስ አበባ የገቡትም ለእስር ተዳርገውበታል፡፡ ይህን በተመለከተም የወያኔ ቅጥረኞችና ሌሎች የሚነዙት ውሸትም እንዲሁ አድማጭ ጆሮ አላገኘም፡፡ ድርጅቱ በቂም በቀል ቢናወዝ ኖሮ ቀደም ጠላት ብሎ ከተዋጋቸው ጋር ሳይቀርበመሆን ኢዴኃቅን መሥርቶ ደርግንም ወያኔንም ባልታገለ ነበር፡፡ ዛሬ የመለስ ቡድን የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን ከእስር ሲፈታ ደርጅቱ ይህን እርምጃ የተቃወመውም በጭፍን የቂም በቀል ስሜት ሳይሆን (ለነገሩ ለዚህም ቢሆን የቀይ ሽብር በደል በቂ መሠረት ነው) ፍትሕ ባለመታየቱና በሕዝብም ደም ላይ በመቀለዱ ነው፡፡

ተደጋግሞ በኢሕአፓ እንደተገለፀው የመለስ ቡድን የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን ከሳሽ/ተፋራጅ ሊሆን የሚችልበት ህጋዊም ሆነ ሞራላዊ መሠረትና ብቃት የለውም፡፡ በቅድሚያ የወያኔ ቡድን ራሱ የደርግን የሕዝብ ድርጅት ጽህፈት ቤት ሰርጎ በመግባት ሆነ መረጃ በማቀበል አያሌ የኢሕአፓ አባላትንና ደጋፊዎችን በትግራይ አስገድሏል፡፡ በመሆኑም ለተካፈለበት ወንጀል ራሱ ለፍርድ ሳይቀርብ የወንጀል ተባባሪዎችን ሊይዝም ሆነ ሊፋረድ የሚችል አይደለም፡፡ ቀይ ሽብር ደግሞ በዋና መልኩ በኢሕአፓ ላይ የተነጣጠረ ነበር እንጂ ወያኔ ዓይነቶቹ ቡድኖች የግርጌ ማስታወሻዎችና የእግረ መንገድ ተጠቂዎች መሆናቸውን ሕዝብ ያውቃል፡፡ ማለትም ዛሬ ወያኔና

ሌሎችም ቀይ ሽብር በእኛ ላይ የተነጣጣረ ነበር የሚሉት ሀሰት ነው ማለት ነው:: ዛሬ የአንዳንድ ድርጅቶች መሪዎች ነን የሚሉትም የቀይ ሽብር ጊዜ የአብዮት ታጣቂዎች፤ የከፍተኛና የቀበሌ ባለሥልጣኖችና የወንጀሉ ተባባሪዎች መሆናቸውን ሕዝብ ገና አልረሳም:: የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ሆነው የትግራይ ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ ምንም ሳይደርስባቸው በወያኔ ድርጅት ውስጥ ዛሬም መኖራቸውም የአደባባይ ምስጢር ነው:: ከዚህ ሌላ ግን ዋናው ነጥብ ከሳሽም፤ ተከራካሪም ፈራጅም መሀሪም ወንጀሉ የደረሰበት ሕዝብ መሆን ሲገባው የሽብሩ ተጠቂዎችና ቤተሰቦቻቸው ሁሉ ከሂደቱ ተገልለው ወያኔና ሹመኞቹ የገነኑበት ይህ ሂደት ህገ ወጥ ነው:: ያንን የግፍና የደም ተመክሮ አያሳርፈወም፤ የሕዝብም ቁስል ለአንዴም ለሁሌም አይሽርም:: እነ ዳሮ ነጋሽ ነፍሰ ጡሯን በግፍ የገደሉትን፤ የብቸና አርሶ አደሮች ያስጨፈጨፈውን፤ አረመኔያዊ ስየልና ግድያ በሕዝብ ላይ የፈፀሙትን ማርኩ ብሎ የለቀቀው የመለስ ቡድን ዛሬም--ከ1983 ጀምሮ--ደርግን በቀራጥነት የታገሉትን የኢሕአፓ መሪዎች (እነ ፀጋዬ ደብተራውን÷ ይሰሐቅን÷ ስጦታውን÷ በለጠን÷ ... ወዘተ) አፍኖ ደብዛቸውን ማጥፋቱን ስናነሳ ነፍስ ገዳዮች ለነፃነት ሀገር ወዳዶች ለጉድጓድ እስር ቤት ይሆንብንና ፤ የግል ጥቅማቸውን ሲያሳድዱ ሀገርን የጎዱት ለሀገር በቅተውና “ንብረታቸው” እየተመለሰላቸው ባለበት ያን አሮጌ ሥርዓት የታገሉት ግን ለሀገራቸውም አንዳይበቁ ታግደው አንዳሉ በምፀት ስንታዘብ ወያኔ በትግልና በሕዝብ ደም መቀለዱ ይቆጠቁጠናል:: ከሕዝብም ፍትህ የማግኘት መብቱን ነጥቋል:: ምሕረት ከተባለም መሀሪ ሕዝብ አንጂ እስር ቤቶቹን በ35 ሺህ የፖለቲካ እስረኞች ያጨናነቀና በእስረኛ ላይ ሁሉ አሰቃቂ ስየል ሲፈፅም የሚታይ ዘረኛ አገዛዝ ሊሆን አይችልም:: ይህ ነው የኢሕአፓ አቅዋም:: ይህ ነው የሕዝብ አቅዋም:: ነገ ተነገ ወዲያ ሕዝብ ግን ለፈሰሰው ደም ተጠያቂዎቹን በሕግ ፊት መፋረዱም የማይቀር መሆኑ ሊታወቅ የሚገባ ሐቅ ነው::

ዓመት አልፎ ሲተካ ኢሕአፓ አልተን÷ አልጠፋ ብሎ ሲገኝ መርዶ የሚሆንባቸው ክፍሎች በመሠረቱ የሕዝብ ጠላቶች ናቸው:: ቀጥሎም የሀገርና የሕዝብን ታሪክ ማወቅ አቅቷቸው በሀሰት ፈረሰ ሽምጥ ማለቱን የመረጡት ክፍሎች ናቸው:: ሐቁ ቢነገር ቢነገር ለሐቁ ጆሯቸው የተደፈነ ወያኔን መሰሎቹ፤ ኢሕአፓ የምሥረታ ወይም የታወጀበትን ዓመቱን አከበረ በተባለ ቁጥር ዛር እንደያዘው ሰው የሚያጓሩት ድርጅቱ ከሌለ ችግራችን አይኖርም ብለው ስለሚያምኑ ነው:: ሕዝብን በቀላሉ እናደናግራለን ብለው የሚያስቡ ሌሎችም ኢሕአፓበመድረኩ ተገኝቶ የተሳሳተ ፖለቲካ መስመራቸውን ማጋለጡን አይወዱትም:: ሕዝብ ማወቅ መንቃቱን መቀበል ስለሚያቅታቸውም ንቀት በተሞላበት ግምገማ ኢሕአፓ ቢጠፋ ኖሮ አቅዋማችንን ሕዝብ ይቀበለው ነበር ብለው ያስባሉ:: ለዚህም ነው ለፖለቲካ ችግራቸው፤ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ለማጣታቸው፤ ለክስረታቸውና ለውድቀታቸው ሁሉ በቅድሚያ ኢሕአፓን የሚከሱት:: ይህ ክስ ደግሞ ይበልጥ አስገራሚ የሚሆነው ከሳሾቹ--ወያኔን ጨምሮ--ኢሕአፓ የሚባል ድርጅት የለም ብለው በየቀኑ ሲምሉ ሲገዘቱ መደመጣቸው ነው - ከሌለ ታዲያ ትዝታው ለምን ይሆን ይህን ያህል የሚያስበረግገው:: ኢሕአፓ ሕልው ለመሆኑና የፃፈውም የጀግና ታሪክ ደማቅና አርዓያ ለመሆኑ ብዙ ምስክር መጥራትን የግድ የሚል አይደለም:: በተለይም ያለውን ተጨባጭ ሁኔታና የድርጅቶችን ይዘትና የትግሉንም ጥራትና ጥንካሬ በተመለከተ ግምግማ ስናካሂድ የኢሕአፓ ሚናና ታሪክ ምንኛ አኩሪ እንደነበርና አንደሆነም መገንዘብ እንችላለን:: ለዚህም ነው ኢሕአፓ

የታወጀበትን (ነሐሴ 26) በየዓመቱ ሲያከብር ይህን አኩሪ ታሪኩን ለማደስ ቃል እየገባና በቅርሱም እየኮራ የሚሆነው:: የድርጅት ህልውናን ጠብቆ ለጥቂት ዓመታት መቆየት እነሆ ለብዙዎች ከባድ ሆኖ እየተፈረካከሱ ባለበት ኢሕአፓ በወያኔና በባዕዳን እና በአንጃዎች የሚቃጣበትን ጥቃት ሁሉ ተቋቁሞ መቀጠሉ የሚደነቅ ሆኖ የሚገኘው::

ኢሕአፓን በአፍራሽነት ጥላሸት ለመቀባት አያሌ ጥረቶች ቢደረጉም ታሪክ የሚመዘግበው ሐቅ ግን ድርጅቱ ሕዝብን አስተባብሮ፤ ሁሉን ኃይሎችን አግባብቶ በጋራ ጠላት ላይ አስነስቶ ድልን ለመቀዳጀት ነበር/ነውም:: በህብረት ሽፍንፍን ፤ በዴሞክራሲ ጭምብል ግን የሀገርን አንድነት ማናጋትን ትላንትም ተቃውሟል፤ ዛሬም ይታገላል:: ወያኔ ለሥልጣን ከመብቃቱ በፊት በግንቦት 1982 ባወጣው የዴሞክራሲያ ዕትሙ ኢሕአፓ የሚከተለውን መልዕክት አስተላልፎ ነበር፡-

> *“ ኢሕአፓ ደግሞ ደጋግሞ በነባራዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብን ሰላም የነሱት፤ መብቱን የነፈጉት፤ ክብሩን የገሠሱት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዳይሸጋገር ድልድዩን የሰበሩበት፤ ሀገር ያሳጡት፤ ፀረ ሰላምና ፀረ ዴሞክራሲ የሆኑት... ዋነኛ ጠላቶቹን አስወግዶ ዴሞከራሲያዊ መንግሥት ለማቆም የሚሹ ዴሞክራሲያውያን ኃይላትና ዴሞክራት ግለሰቦች ሁሉ፤ አንተ ከበርቴ ነህ፤ አንት ምንትሴ ነህ፤ ...ወዘተ የሚል መገርገርያ ደንቃራ ሳይሆንባቸው፤ ከሀገር አጥፊ ጠላቶች አገርን ከማላቀቅ አንፃር ሲታዩ ኢምንት የሆኑ የማያግባቡ ልዩነቶችን ወደ ጎን ትቶ፤ የጋራ ፕሮግራም ነድፈው በአንድ የህብረት ግንባር ስር በጋራ ጠላቶቻቸው ላይ መሠለፍ አለባቸው ይላል:: እዚያም ላይ አያቆምም:: ጠላት በጋራ ትግል ከወደቀ በኋላ እንደ ሕፃናት “ጨዋታ ፈረሰ፤ ዳቦ ተቆረሰ” ተባብሎ የየራስን ልዩነት ወደ አፋፍ በማምጣት፤ ሀገር የምትመራው በኔ የፖለቲካ መስመር ነው፤ በዚህኛው ርዕዮተ ዓለም ነው፤ የለም በዚህኛው ነው የሚል አምቧጓሮ አብቅሎ ደምሳሽና ተደምሳሽ ተኳኩኖ እንደገና ያው የተጠናወተ በሽታ የሚያገረሽበትን “የታጥቦ ጭቃ” አካሄድ መከተል ሳይሆን፤ በጋራ ሁኖ የሽግግር መንግሥት ማቋቋምና ሠፊው ሕዝብ በዴሞክራሲ መብቱ ላይ ገደብ ሳይበጅበት በፈቀደው ሊደራጅ፤ ያሻውን የፖለቲካ መስመር፤ ያፈተተውን ርዕዮተዓለም ሊያንፀባርቅ፤ ሊሰብክ፤ ሊያስተምር፤ በጸሐሁም ሊረጭ የሚችልበትን ዴሞክራሲያዊ መድረክና የተመቻቸ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለመፍጠር እጅና ጓንት ሁነው አብረው በመሥራት የሚሳተፉበት ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንዲቋቋም መሠረቱን ማንጠፍ አለባቸው ይላል::”*

ይህ ምክርና ማሳሰቢያ ግን ትላንትም አልተደመጠም፤ ዛሬም በሚገባ ሊረዱት ያልቻሉ አሉ:: በሕዝብ መብት ላይ ገደብ መደረግ የለበትም፤ በጋራ እንታገል፤ ...ወዘተ የሚሉት አቅዋሞች ሆኑ የሽግግር መንግሥት ይመሥረት የሚለውም ቢሆን ለኢትዮጵያና በኢትዮጵያ የሚለውን መሠረት ያደረገ ነው:: ኢሕአፓ በሂደት ከመርህ ግብር አንፃር ጊዜው የሚጠይቀውን ለውጥ ያደረገ ቢሆንም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ግን መቸም ድርድር አልገባም:: በሕዝባዊነቱ፤ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ማስቀደም በሚለው ላይም ለውጥ አላደረገም:: ኢሕአፓ ዛሬምቢሆን

ትግሉ ለጥቂቶች፥ ለምርጦች ሳይሆን ለሰፊው ጭቁንና ሰርቶ አደር ሕዝብ ነው። ኢሕአፓ ትግሉ ጨዋታ ፈረስ ዳቦ ተቆረሰ ዓይነት ሀገርን በመጨረሻ ለቅርጫ ለማቅረብ ሳይሆን የሀገርን አንድነት ለማስከበር ነው። ለዚህም ነው ኢሕአፓ ዴሞክራሲ ሲል ሀገርን የማፍረስ መብት ወይም በቅርቡ እየተደመጠ ያለውን ባፈተተን እንሂድ እንገነጣጠል አጓጉል አቅዋምን ቡራኬ ለመስጠትም አይደለም። በጋራ ትግል የሚመሠረት የጋራ የሽግግር መንግሥትም፥ ኢትዮጵያን አንድነቷን ጠብቆ ለዴሞክራሲ ሽግግር የሚያደርሳት እንጂ ለመበታተን የሚያመቻቻት ሊሆን አይገባውም/አይቻልምም። ኢሕአፓ 39 ዓመት በፊት ሲመሠረትም ይዞት የተነሳው አቅዋም ለኢትዮጵያ እንጂ ሌላ አልነበረም። ለዚህም ነው የወያኔ ሁሉም ይገንጠል የ1967 ጦማር (ማኒፌስቶና) የኤርትራ ድርጅቶችን “ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት” የሚለውን ሆነ ከሲሶ በላይ የኢትዮጵያን መሬት ምዕራብ ሶማሊያ ነው ያለውን ባሬን አልቀበልም ብሎ፤ በነዚህ ሁሉ ኃይሎች ጥቃትና ጉዳት የደረሰበት። ዛሬ ከስንት ዓመታትና መስዋዕትነት በኋላ ኢሕአፓ ኢትዮጵያን የሚጎዳ አቅዋም ይዞ ሊሰነጣጥቋት ለሚፈልጉ መሣሪያ ሊሆን አይታሰብም።

ወያኔ በኢሕአፓ ላይ የከፈተው ከፍተኛ የስም ማጥፋትና የጥቃት ዘመቻ በቅጥረኞቹ አማካይነት በአሁኑ ጊዜ ሊፋፋም እየሞከረ ነው። ሞት ሳይቀር መፈራገጥ መባል ያለበትም ነው -ዘረኛው አገዛዝ ጊዜው ሊጨልምበት መድረሱ ሊካድ የሚችል አይደለምና! አገዛዙ በሁሉምመስክ ክስረት እያጋጠመው መግዛትና በሥልጣን መቆየትም የቻለው ወይም እየቻለ ያለው አፈናውን በማጠናከር ብቻ ነው። ይህ የውድቀቱ ምልክት ነው--የሕዝብን ድጋፍ ሊያገኝ አልቻለምና። በአንድነት ኃይሎች ላይ--ይድከሙ አይጠንክሩ ዛሬም አሉ-- የጥፋት ዘመቻውን ማጠናከሩ የድክመቱ ምልክት ነው። ይህን የወያኔ አገዛዝ ዘመቻ በዚህም በዚያም እያጀቡ ግን ራሳቸውን የሕዝብ ጎራ ነን ሊሉ የሚቃጡም አልጠፉም። ገለባውን ከእንክርዳዱ ለመለየት ዛሬም ነቅቶና ቆርጦ መነሳት ያስፈልጋል ማለት ነው። ህብረትም በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ለኢትዮጵያ መሆን አለበት ሲል ኢሕአፓ ጫና ሰጥቶ አቅዋሙን የሚያቀርበው አለምክንያት አይደለም። ካለፈው ተመክሮ በመማርም ሆነ ሁኔታው ግድ ብሎ ያሳለፍነውንና የፈፀምነውን ስህተት ላለመድገም መጣር ግዴታችን ነው። ኢሕአፓ የታወጀበትን ሲያከብርና አዲስ ዓመትን ተቀብሎ ቃል ኪዳኑን ሲያድስ መሠረት የሆኑትንም መርሆዎቹን--ለሰፊው ሕዝብና ለኢትዮጵያ አንድነት፤ ለዴሞክራሲ መቆምን--ሳይቀይር፥ ሳይለውጥ ይዞና ከዚህ በፊትም ታሪክን በደማቅ ፅፎ እንዳረጋገጠው ለመስዋዕትነትም ዝግጁ ሆኖ ነው።

ለሀገር መሞት ሕይወት
ዳግም ትንሳዔ ልደት
ይላል አሁንም ኢሕአፓ።

በወያኔ አገዛዝ ላይ ድልን ለመቀዳጀት ተባብረን እንታገል!
እናቸንፋለን !